City of Seattle




# የሲያትል የኤሌክትሪክ ጭነት መኪና ማበረታቻ የሙከራ ፕሮግራም

**ሲያትል፣ የኤሌክትሪክ ጭነት መኪና ኤሌክትሪፊኬሽን ማበረታቻ ፓይለት ፕሮግራም የሚባል አዲስ ፕሮግራም አላት። የኤሌክትሪክ ጭነት መኪናዎችን መጠቀምን ያበረታታል እና በሲያትል ወደብ ለሚጠቀሙ አዳዲስ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ቅናሾችን ይሰጣል። የታዳሽ ኃይል አጠቃቀምን ያበረታታል እንዲሁም ጎጂ ልቀቶችን ለመቀነስ ይረዳል።**

**ማበረታቻው የአንድ የኤሌክትሪክ ጭነት መኪና ዋጋ 40% ይከፍላል። ይኸውም ለአንድ ትራክ እስከ 180,000 ዶላር የሚደርስ ይሆናል።**

## ጎጂ የጤና ልዩነቶችን እና የአየር ንብረት ብክለትን መፍታት

በሲያትል ዱዋሚሽ ሸለቆ ውስጥ ያሉ የማህበረሰብ ድርጅቶች ከኢንዱስትሪ፣ ከናፍታ መኪናዎች፣ እና ከትራንስፖርት የሚለቀቁትን ብክለቶች ለመቀነስ የኤሌክትሪክ ጭነት መኪናዎች ስራ ላይ እንዲዉሉ ግፊት ያደርጋሉ። ጥናቶች እንደሚያሳዩት በወደቡ አቅራቢያ ያሉ ሰፈሮች፣ ቤከን ሂል፣ ጆርጅታውን፣ እና ደቡብ ፓርክን፣ ጨምሮ በሲያትል ከሚገኙ ሌሎች አካባቢዎች ጋር ሲነፃፀሩ ከፍተኛ የአየር ብክለት እና እንዲሁም በልጆች ላይ ከፍተኛ የአስም መጠን አላቸው።

### የመጓጓዣ ልቀትን ለመቀነስ የሲያትል ግቦች

| 30% | 82% | 2050 |
|---|---|---|
| በ2030 30% ዜሮ ኢምሽኖች ይደርሳሉ | በ2030 የ82% ልቀትን መቀነስ | ካርቦን ገለልተኛ በ 2050 እ.ኤ.አ |

## ለምን የጭነት መኪናዎች?

የሲያትልን እና የታኮማን ወደቦች ለማገልገል **የወደብ ስራ በግምት ወደ 4,000 በሚሆኑ የናፍጣ መኪናዎች የሚወሰን ይሆናል።**

**በናፍታ የሚንቀሳቀሱ መኪኖች** በአካባቢው ከፍተኛ ብክለትን ያስከትላሉ። ሞተሮቻቸው ጎጂ የሆኑ ቆሻሻዎችን በአካባቢው ሰፈሮች፣ በዳዉንታዉን ሲያትል፣ እና በዱዋሚሽ ሸለቆ ውስጥ ይለቃሉ።

የአካባቢ ፍትህ ማህበረሰቦችን ተጠቃሚ ለማድረግ **ሲያትል የናፍታ ልቀትን ለመቀነስ ቅድሚያ ትሰጣለች።**



# እንዴት ማመልከት እንደሚቻል




**የማመልከቻው ሂደት ከታች አለ። ለተጨማሪ ዝርዝሮች እባክዎ የእኛን "How to Apply Guide" (እንዴት ማመልከት እንደሚቻል መመሪያን) ይመልከቱ። ለማንኛውም ጥያቄ፣ ለእርዳታ OSE_Trucks@seattle.gov ያግኙ።**

**ደረጃ 1: የፕሮግራም ብቁነትን እና መስፈርቶችን ይገምግሙ**
በፕሮግራሙ መመሪያ ወይም በድረ-ገጹ ላይ ያለውን የብቃት መስፈርት በመገምገም ብቁ መሆንዎን ይመልከቱ።

**ደረጃ 2: አስፈላጊ ሰነዶችን እና መረጃዎችን አዘጋጅ**
ሁሉንም ሰነዶች እና መረጃዎች ይሰብስቡ።

**ደረጃ 3: የማመልከቻውን ቅጽ ይጎብኙ**
የኤሌክትሪክ ጭነት መኪና ማበረታቻ ፓይለት ፕሮግራም ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽን ይጎብኙ።

**ደረጃ 4: የማመልከቻ ቅጹን ይሙሉት**
ማመልከቻውን በትክክለኛ፣ እና ዝርዝር መረጃ ይሙሉ። ሁሉንም አስፈላጊ ሰነዶችን እና መረጃዎችን ያቅርቡ።

**ደረጃ 5: ማመልከቻውን ያስገቡ**
ማመልከቻዎን አንዴ ከገመገሙ በኋላ በድረ-ገጹ ቅፅ ላይ ያቅርቡ እና አባሪዎችን በOSE_Trucks@seattle.gov ኢሜል ያድርጉ።

**ደረጃ 6: የማመልከቻ ማጣራት እና ግምገማ**
ከቀረበ በኋላ፣ ማመልከቻዎች ይጣራሉ እና ይገመገማሉ። የማመልከቻው ጊዜ ካለቀ በኋላ ስለ ሁኔታው ማሳወቂያ ይደርስዎታል።

**ደረጃ 7: ቀጣይ እርምጃዎች እና እርዳታ**
ማመልከቻዎ የተሳካ ከሆነ፣ ማንኛውንም ተጨማሪ መስፈርቶችን ጨምሮ ወደ ፕሮግራሙ ለመቀጠል፣ በሚቀጥሉት ደረጃዎች መመሪያዎች ይደርስዎታል። ማመልከቻዎ ካልተሳካ፣ ስለወደፊቱ የገንዘብ ድጋፍ እድሎች ልናገኝዎ እንችላለን።

**ወደፊት ለማመልከት ይፈልጋሉ?**
**የእኛን የፍላጎት ቅጽ ይሙሉ!**